22ኛ ዓመት ቁጥር 13
22th Year No. 13

ባሕር ዳር ነሐሴ 19 ቀን 2010 ዓ.ም
Bahir Dar, August 25, 2018

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Region in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 45 ብር
Unit Price Birr 45

## ማውጫ


*አዋጅ ቁጥር 254/2010 ዓ.ም*

**የአማራ ብሔራዊ ክልዊ መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ**


## Content


*Proclamation No. 254/2018*

**The Amhara National Regional State Executive Organs Establishment and Determination of their Powers and Duties Re-amendment Proclamation**


## አዋጅ ቁጥር 254/2010 ዓ.ም

### የአማራ ብሔራዊ ክልዊ መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የክልሉ ሁለንተናዊ እድገት ዘለቄታ ያለው ሆኖ ይቀጥል ዘንድ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚካሄደውን መዋቅራዊ ሽግግር እውን ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በግብርና ላይ የተመሰረተውንና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የክልሉን የኢንዱስትሪ ልማት ለማፋጠን ይቻል ዘንድ የዘርፉ አደረጃጀት ከሌሎች የሥራ እንቅስቃሴዎች ጋር መጣመሩ ቀርቶ ራሱን በቻለ አስፈፃሚ አካል ስር እንዲመራ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

## Proclamation No. 254/2018

### A Re-amendment Proclamation Issued to provide for the Establishment and Determination of their Powers and Duties of the Amhara National Regional State Executive Organs

WHEREAS it is found necessary to realize the structural transformation that is being taken place in the Economy so as to the region's overall development sustains;

WHEREAS it is necessary to make the sector's structure, which was inclusive with other works, to be led by independent executive organ in order to foster the region's industry development that is based on agriculture and found at a low level;

የገጠር ኢንዱስትሪን በማስፋት በአመዛኙ በእርሻና በእንስሳት ሃብት ልማት ላይ ጥገኛ ሆኖ የቆየውን የክልሉን ኢኮኖሚ ወደላቀና ዘርፈ ብዙነት ወዳለው ደረጃ ማሸጋገርና ለዜጐች አማራጭ የሥራ እድል የሚፈጠርበትን ሁኔታ ማመቻቸት ተገቢ በመሆኑ፣

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ድንጋጌ ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

## *1. አጭር ርዕስ*

ይህ አዋጅ “የተሻሻለው የአስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 254/2010 ዓ.ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## *2. ማሻሻያ*

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 230/2008 ዓ.ም እንደሚከተለው በዚህ አዋጅ ተሻሽሏል፡-

ሀ. የአዋጁ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (2) ከተሰረዘ በኋላ ከንዑስ አንቀጽ (1) ቀጥሎ የተመለከቱት ሁለት አዳዲስ ንዑሳን አንቀፆች (2) እና (3) የገቡ ሲሆን በዚሁ ምክንያት ከንዑስ አንቀጽ (3) እስከ ንዑስ አንቀጽ (17) የሰፈረሩት ድንጋጌዎች ከንዑስ አንቀጽ (4) እስከ ንዑስ አንቀጽ (18) ሆነው ወደ ፊት ተሸጋሽገዋል፡-

(2) የኢንዱስትሪ ቢሮ፣

WHEREAS it is appropriate to facilitate to transform the region’s Economy that stayed mostly dependent on agriculture to a greater and multidimensional level and animals resource development in rural to promote industrialization, and to promote job opportunities to citizens;

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region in accordance with the powers vested in it under Article 49 sub-article 3 (1) of the revised Constitution of the National Regional State hereby issued this proclamation.

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as “The Revised Executive Organs Establishment Proclamation Amendment Proclamation No.254/2018.”

## 2. Amendment

The Revised Amhara National Regional State Executive Organs Establishment and Determination of their Powers Proclamation Number 230/2015 is amended with this proclamation as follows:

**A.** After the cancealation of Article 10 sub-article (2) of the proclamation, whereas two new sub-articles (2) and (3) are added next to sub-article (1), due to this, the provisions put from sub-article (3) upto sub-article (17) are forwarded from sub-article (4) upto sub-article (18).

(2) Industry Bureau;

(3) የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ

ለ. የአዋጁ አንቀጽ 15 ከተሰረዘ በኋላ ከአንቀጽ 14 ቀጥሎ የሚከተሉት ሁለት አዳዲስ አንቀጾች 15ና 16 የገቡ ሲሆን በነዚሁ ተጨማሪ አንቀጾች መካተት ምክንያት ከአንቀጽ 16 እስከ አንቀጽ 39 የሰፈሩት የአዋጁ ቀደምት ድንጋጌዎች ከአንቀጽ 17 እስከ አንቀጽ 40 ሆነው ወደፊት ተሸጋሽገዋል፦

## 15. የኢንዱስትሪ ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ኢንዱስትሪ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በክልሉ ውስጥ የሚካሄደውን የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት እንቅስቃሴ የአገሪቱን ፖሊሲና ስትራቴጅ መሠረት በማድረግ ያለማል፣ የክልሉን የኢንዱስትሪ ስትራቴጅ ይቀርፃል በክልሉ መንግሥት ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
2. በክልሉ ውስጥ የኢንዱስትሪ ተቋማት እንዲያብቡና እንዲስፋፉ ይደግፋል፣ ያበረታታል፣ የጥናት፣ የስልጠና፣ የቴክኒክና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፣
3. በክልሉ ውስጥ አምራች ወይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት ማነቆ የሆኑ ችግሮችን እየለየ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልልና የፌዴራል መንግስት አካላት ጋር በመተባበር እንዲፈቱ ያደርጋል፡፡

(3) Trade and Market Development Bureau

B. After Article 15 of the proclamation being cancealed, whereas the following two new articles 15 and 16 are added next to Article 14, because of this the previous provisions of the proclamation put from article 16 upto Article 39 are forwarded from Article 17 upto article 40.

## 15. Industry Bureau

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Industry Bureau shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1. Develops the activities of manufacturing industry taken place in the region in line with strategies and polices of the country; designs the industrial strategy of the region and applies when it is approved by the regional government.
2. Supports and encourages for the flourishment and expansion of industrial institutions in the region; gives a research, training, technical and advisory services; follows up its success.
3. Makes problems_by identifying, which are obstacles for promoting manufacturing industries in the region, to be solved in collaboration with concerned regional and federal bodies.

4. ከክልሉ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር በመተባበር የኢንዱስትሪ ፕሮጀክት ሃሳቦችን በየጊዜው እያመነጨ ሊጠኑና በሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባቸውን በመለየት አግባብ ላለው የፌዴራል መንግሥት አካል ያስተላልፋል፣ በክልሉ አቅም ሊፈፀሙ የሚችሉት ደግሞ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

5. የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉን በመደገፍ ረገድ ቁልፍ ሚና ካላቸው የክልሉና የፌዴራሉ አስፈፃሚ አካላትም ሆነ የከፍተኛ ትምህርትና ምርምር ተቋማት ጋር የጋራ ዕቅዶችን አውጥቶ ይሠራል፣ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

6. አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ለሚሰማሩ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ የኢንዱስትሪ መንደሮችን፣የክላስተር ማእከላትንና የኢንዱስትሪ ልማት ፓርኮችን ያደራጃል፣ ለነዚሁ የሚያስፈልገው መሬት ከሦስተኛ ወገኖች ይዞታ ነፃ እንዲሆን ያደርጋል፣ የቦታ ካርታና ፕላን በማሠራትም ሆነ እስከየመዳረሻቸው የሚዘልቅ መሠረተ-ልማት እንዲሟላላቸው በማድረግ ያስተዳድራል፣ እንዳስፈላጊነቱ ለኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ያስተላልፋል፡፡

4. Having, from time to time initiated industrial project ideas, duly identifies those requiring examination and implementation and conveys to pertinent bodies of the federal and regional governments as well as cause the implementation of those projects capable of being materialized with the capacity of the region, in collaboration with the regional investment commission.

5. Work for by issuing communal plans with the regional and federal executive bodies as well as with the higher education and research institutions those have a great contribution with regard to supporting the manufacturing sector; follows up and supports.

6. In collaboration with pertinent government bodies, organizes industry zones, cluster centers and industry development parks which can be used for manufacturing industry services for those who engage in the manufacturing sector in the region; makes the land free from third party for this service; administers causing to be prepared map and plan of the plot as well as to be fulfilled infrastructures extending to their destinations; transfers to industry parks development corporation as its necessity.

7. የገጠር ኢንዱስትሪን ለማስፋፋት በያካባቢው ያለውን የመልማት አቅም መሠረት ያደረገ የኢንዱሰትሪ ዓይነትቶችን ይለያል፣ እንዲስፋፉ ድጋፍ ይሰጣል፡፡
8. በክልሉ ውስጥ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ሁለንተናዊ አቅም ለማሳደግ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ይሰጣል፣ የድጋፍ ማእቀፎችን ያዘጋጃል፡፡
9. በጠቅላላ የጥራት አሠራርና አስተዳደር እንዲሁም በድርጅቶች መካከል በውል ሊፈጠር ስለሚችል የሥራ ቁርኝት አሠራር ያስተዋውቃል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፡፡
10. የአምራች ኢንዲስትሪያሊስቶች አቅም የሚገነባባቸውን ተቋማትን ያደራጃል፣ ይደግፋል፣ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረጊያ ሆነው እንዲያገለግሉ ያደርጋል፡፡
11. ለአምራች ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ዘላቂ ፋይዳ ያለው የአዋጭነት ጥናትና የፕሮጀክት ትግበራ፣ ክትትልና ድጋፍ ስርአት ቀርፆ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
12. ከአምራች ኢንዲስትሪው ዘርፍ በኩል የሚቀርቡለትን ፕሮጀክቶች ይቀበላል፣ ወደየክላስተር ማእከላት፣ የኢንዱስትሪ መንደሮች ወይም ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ሊገቡ የሚችሉትን ይለያል፣ የየፕሮጀክቶቹን ፕላንት ሌይ-አውት ይገመግማል፣ የሚያስፈልጋቸውን የመሬት መጠን ይወስናል፣ ለፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ያስተላልፋል፡፡



7. Identifies kinds of industry based on the development capacity of an area to expand rural industry; gives support to be expanded.
8. Gives industry extension services in order to enhance the all-rounded capacity of manufacturing industries in the region; prepares support frameworks.
9. Advertises about a general quality procedures and administration as well as working relationship procedures that will be created on contracts between and among organizations; gives support and approves their success.
10. Organizes institutions that will enhance the capacity of manufacturing industrialists; supports; makes them to be served as a means of knowledge and transfer of technology.
11. Designs a cost-benefit analysis and project implementation, supervison and support system that has a sustainable relevance for the the expamnasion of manufacturing industries, and cause to be implemented.
12. Receives projects submitted from the sector of manufacturing industries; identifies those can be entered to cluster centers, industry zones or industry parks; evaluates the layout of each project plant; determines their demand of land; and transfers to the parks development corporation.

13. ወደ ክላስተሮች፣ የኢንዱስትሪ መንደሮችና ፓርኮች የገቡ ፕሮጀክቶችን ውጤታማ እንደሆኑና በተቀመጠው ጊዜ ወደ ሥራ እንዲገቡ ለማድረግ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ ያሉባቸውን ችግሮች በመለየት ይፈታል፣ አስፈላጊውን እርምጃም ይወስዳል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፡፡
14. ዘላቂ የኢንዱስትሪ ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችል የአካባቢ ጥበቃና ደህንነትን በዘላቂነት ሊያሰጠብቅ በሚችል መልኩ ልማቱን ይመራል፣ ይደግፋል፡፡
15. ኢንዲስትሪያሊስቶችን ለመፍጠር ወይም ያሉትን ለማጠናከር የሚረዳ ክልል-አቀፍ የኢንተርፕሬነርሽፕ ፕሮግራም ቀርፆ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ስልጠናዎችን ይሰጣል፡፡
16. የክልሉ የኢንዱስትሪ ምርቶች በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሃገር በገበያ እድል እንዲያገኙ አቅዶ ይሠራል፣ እንቅስቃሴዎችን ያስተባብራል፡፡
17. የአምራች ኢንዱስትሪዎች የዘርፍ ማኀበራት እንዲደራጁ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ተከታታይ ድጋፍ በማድረግ ውጤታማ ያደርጋል፡፡



13. Supervises and supports projects those entered to clusters, industry zones and parks so as to make them to be productive and engage to work in time; solves their problems –by identifying; takes the necessary measures and approves its productiveness.
14. Leads and supports the development in a way that can enable to preserve environmental protection and well-being so as to ensure sustainable industrial development.
15. Implements _by designing a regional-wide enterpreneurship program that can enable to create industrialists or to strengthen the existing ones; and gives trainings.
16. Works by planning to make the regional industry products get chance in the local as well as abroad markets; and collaborates their activities.
17. Makes the necessary support for manufacturing industry sector associations to be organized; and makes them to be productive by making successive support.

18. የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት የሚረዱ ምርጥ ተሞክሮዎችን ያሰባስባል፣ ይቀምራል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤
19. ለአምራችኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጋቸውን የፋይናንስ፣ የትራንስፖርት፣ ትራንዚት አገልግሎትና ሌሎች የድጋፍ ሥራዎችን ይሰራል፡፡

## *16. የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ*

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በክልሉ ውስጥ የሚካሄደው ማናቸውም የንግድ እንቅስቃሴ በሃገሪቱ የንግድ ፖሊሲ፣ ህግና ደንብ መሠረት መከናወኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ህጋዊነት ያለውና ስነ-ምግባር የተላበሰ የንግድ አሠራር እንዲከበር ያደርጋል፣ ህገ-ወጥ የንግድ አሠራሮችን ይከላከላል፡፡

2. የሃገሪቱን የንግድ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች መሠረት በማድረግ በክልሉ ውስጥ የንግድ ተቋማት እንዲስፋፉ ያበረታታል፣ የጥናት፣ የስልጠና፣ የቴክኒክና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልልና የፌዴራሉ መንግሥት አካላት ጋር በመተባበር በዘርፉ የሚታዩ ማነቆዎች እንዲፈቱ ያደርጋል፡፡



18. Collects, makes and distributes, to users, best practices those help to promote manufacturing industries.
19. Works for finance, transport, transit services and other supports needed by manufacturing industries.

## 16. Trade and Market Development Bureau

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Trade and Market Development Bureau shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1. Follows up and supervises the conduct of any trade activities undertaken in the region pursuant to the national trade policies, laws and regulations; causes the observance of lawful and ethical trade activities, and prevent the undertaking of those activities in an illegal manner.
2. Encourages the promotion of trade institutions in the region on the basis of trade policies and strategies of the country; render the study, training, technical and advisory services, and causes the resolutions of outstanding difficulties in the sector through follow up of same in collaboration with the pertinent federal and regional bodies.

3. በክልሉ ውስጥ በንግድ ሥራ የሚሰማሩትን የሃገር ውስጥ ባለ ሃብቶች በንግድ ሕጉ መሠረት ይመዘግባል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፡፡
4. በክልሉ ውስጥ በትርፍ ሥራ ላይ የተመሠረተ ዓላማ ይዘው የሚንቀሳቀሱ የንግድ ማኅበራትን መመስረቻ ጽሁፎች፣ መተዳደሪያ ደንቦችና የእነዚህኑ ማሻሻያዎች ተቀብሎ በመመርመርና ሕጋዊነታቸውን በማረጋገጥ ይመዘግባል፡፡
5. የክልሉን የንግድ መዝገብ ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፣ የነጋዴዎችን የተሟላ መረጃ ይይዛል፡፡
6. የገበያና የንግድ ሥራ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማጠናቀር፣ በመተንተንና በማሰራጨት ረገድ ተፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ የገበያ ትስስር እንዲኖር ያደርጋል፡፡
7. የግብይት ልማት ዘርፉን ለማጠናከር በተመረጡ መስኮች ለክልሉ የግብይት ተዋናይ የብድር አገልግሎት ያመቻቻል፡፡
8. በክልሉ ውስጥ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት እንዲሁም የእነዚሁ ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ በንግድ አሠራር ረገድ ያላቸው ግንዛቤና ተሳትፎ እንዲዳብር ያደርጋል፡፡

3. Registers, pursuant to the commercial laws, issues and renews license to those domestic investors will be engaged in trade activites throughout the region; as well as collects the appropriate service fees.
4. Registers by investigating and assuring its legality of the submitted by-laws, regulations and their own revisions of the trade societies who perform based on the objective of profit making trade in the region.
5. Establishes and administers the regional book of trade and thereby maintain the complete profile of traders therein.
6. Provides the necessary support with regard to the collection, compilation, analysis and distribution of market and business related information and thereby causes the creation of marketing ties.
7. Facilitates a credit service for the regional marketeers to sterengthen the market development sector being selected.
8. Encourages and supports the establishment, in the region, of business and sector associations and their respective councils as well as promote their awareness and participation in respect of business procedures.

9. የክልሉን ምርቶችና አገልግሎቶች ለማስተዋወቅ የሚረዱ ቋሚ ኤግዚቢሽኖች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ለሚያዘጋጁ አካላት ድጋፍና ፈቃድ ይሳጣል፣ በሌሎች ክልሎች ኤግዚቢሽኖች ላይ ይሳተፋል፡፡

10. የዋና ዋና የግብርና ምርቶችና ግብይቶች የገበያ ፍላጐት ትንበያ ጥናት ያካሂዳል፣ ይቆጣጠራል፡፡

11. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለግብርና ምርቶች የገበያ ማዕከላት እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የግብይት አማካሪ ምክር ቤት እንዲቋቋም ያደረጋል፣ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

12. የግብርናም ሆነ የኢንዱስትሪ ውጤቶች የጥራት ደረጃቸው ተጠብቆ ለገበያ የሚቀርቡበትን ስርዓት ይዘረጋል፣ ይከታተላል፡፡

13. አይነታቸውና የዋጋ ዝርዝራቸው በፌዴራል የንግድ ሚኒስቴር የሕዝብ ማስታወቂያ ክፍል የተገለፀው ወይም የሚገለፀው የንግድ እቃዎችና አገልግሎቶች በክልል ውስጥ ስለሚሰራጩበት ስለሚሸጡበትና ከቦታ ቦታ ስለሚዛወሩበት ሁኔታ ይወስናል፣ እንዳስፈላጊነቱ እቃዎች ባለቁ ጊዜ እንዲተኩ ለነጋዴዎች መመሪያ ሊሰጥ ይችላል፡፡



9. Causes the preparation of standing exhibitions whereby the regional products and services might be displayed; renders support and license to those bodies preparing same, and participates in such exhibitions which are organized by other regions.

10. Undertakes and monitors market demand forcast studies with regard to those major agricultural products and inputs.

11. Facilitates, in collaboration with concerning bodies of the issue, conditions for the creation and strengthening of market centers for agricultural products; establsishes and thereby supports marketing advisory council.

12. Sets and follows up a system whereby agricultural and industrial outputs may be offered for marketing with their quality standard having been maintained thereto.

13. Determines the distribution, shall be sold and to transfer from place to place in the region, of trade materials and services which their lists of items and prices are specified and will be specified by the Federal Trade Ministry public notice; and as deemed as necessary, it may order merchants to replace when materials are finished.

14. የሸማቹን መብት ለማስከበር የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችንና ለነዚሁ ሲባል የሚፈጠሩ አደረጃጀቶችን ይደግፋል፣ ያስተባብራል፡፡
15. በንግድ ውድድርና በሸማቾች መብት አጠባበቅ ረገድ የሚነሱ አለመግባባቶች በድርድር ወይም በእርቅ እንዲፈቱ የሚያስችል የአሠራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡
16. የንግድ ስርዓቱንና ሸማቹን ሕብረተሰብ የሚጐዱ የተለያዩ ህገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ይቆጣጠራል፣ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
17. ከንግድ አሠራርና ሸማቾች መብት ጋር በተያያዘ ሊፈፀሙ የሚችሉ ወንጀሎችንና ፍትሐብሔር ነክ ጉዳዮችን የሚከታተል የራሱን ዐቃቤ ሕግ የሥራ ክፍል ያደራጃል፡፡
18. ሕገ-ወጥ የንግድ አሠራሮችን ለመቆጣጠርም ሆነ ከዚሁ ጋር ተያይዘው የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በመመርመርና የሚወስዳቸውን አስተዳደራዊ እርምጃዎች በማስፈፀም፣ እንዲሁም ለምስክሮች መጥሪያ በማድረስ ረገድ የክልሉን የፖሊስ ኃይል ሊጠቀም ይችላል፡፡



14. Supports and collaborates the activities and organizations that cause to respect the perchaser’s right.
15. Establishes a work procedure that enables to resolve negotiation, which shall be raised on observance of the trade competition and purchesers’ right, by agreement or arbitration.
16. Supervises different illegal trade activites that shall harm the trade system and purchasing society, and takes administrational and legal measures.
17. Shall organize its own prosecutor that follows up crimes to be performed in relation to trade procedure and purchesers’ right and civil cases.
18. May use the regional police to control illegal trade systems, to investigate crimes that shall be performed regarding this as well as cause to implement administrational measures that it takes and addresses summon to witnesses.

19. ከንግድ ውድድርና የሸማቾች መብት አጠባበቅ አስመልክቶ የሚነሱ ፍታብሔር ነክ ጉዳዮችን ተቀብሎ የማየትና የመዳኘት ሥልጣን የሚኖረው አስተዳደራዊ ፍ/ቤት ሊያቋቁም ይችላል፡፡

20. በኢፌድሪ የወንጀል ሕግ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት እና በሌሎች ሕጐች ከንግድ አሠራርና ሸማቾች መብት ጋር ተያይዞ የሚፈፀሙ የወንጀል ጉዳዮችን የመመርመር፣ የመክሰስ እና ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የመከራከር ሥልጣን ለቢሮው ተሰጥቷል፡፡

21. በንግድ አሠራር እና ሸማቾች መብት ላይ ወንጀል ተፈፅሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ እንዲደረግ ያዛል፣ በቂ ምክንያት ሲኖረው የተጀመረውን ምርመራ እንዲቆም ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲከናወን መመሪያ ይሰጣል፣ በሕግ መሠረት የወንጀል ክስ ይመሠርታል፣ ያነሳል፡፡

ሐ. በአዋጁ አንቀጽ 31 (በዚህ አዋጅ መሠረት አንቀጽ (32) ሆኖ እንደ ተሻሻለ) ከንዑስ አንቀጽ (3) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (4) የገባ ሲሆን በዚሁ ተጨማሪ ድንጋጌ መካተት ምክንያት ከንዑስ አንቀጽ (4) ጀምሮ እስከ ንዑስ አንቀጽ (11) የሰፈሩት የአዋጁ ቀደምት ድንጋጌዎች ከንዑስ አንቀጽ (5) እስከ ንዑስ አንቀጽ (12) ሆነው ወደፊት ተሸጋሽገዋል።

19. May establish administrative tribune that shall have a power to see and judge on civil cases raised, by receiving same, concerning to trade competition and purchesers' right of protection.

20. The power of investigation, sue and pleading is to the Bureau concerning to criminal cases that shall be implemented on the trade's and purchaser's right by the Ethipian Federal Democratic republic of the criminal law, criminal procedure code and by other laws that submit to have court power.

21. Orders investigation to be done where it believes a crime has been excuted on trade procedure and purchaser's right; renders directives the commenced investigation to be stopped or additional investigation to be done where it has a sufficient ground; charges and suspends crimal case pursuant to law.

c. In the proclamation Article 31 (as being amended as Article (32) in this proclamation), where as the following new sub-article (4) is inserted next to sub-article (3), due to this the previous provisions of the proclamation listed from sub-article (4) upto sub-article (11) are forwarded from sub-article (5 ) upto sub-article (12).

3. የክልሉ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፓሬሽን ተጠሪነቱ አዲስ ለተቋቋቋመው የኢንዱስትሪ ቢሮ ይሆናል።

3. The Regional Industry Parks Development Corporation shall be accountable to the newly established Industry Bureau.

### 3. አዋጁ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

### 3. Effective Date

This proclamation shall come into force as of the date of its official publication on the Zikre-Hig Gazette of the Regional state.

**ባሕር ዳር**
**ነሐሴ 19 ቀን 2010 ዓ.ም**
**ገዱ አንዳርጋቸው**
**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዘዳንት**

**Done at Bahir Dar,**
**This 25th day of August, 2018**
**Gedu Andargachew**
**President of the Amhara National Regional State**.